የሰ/መ/ቁ. 47935

ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ግርማ ወልደማሪያም ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እየሩሣሌም ወንዴ ጠበቃ አቶ የሺጥላ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ 12,500 የአሜሪካን ዶላር ይዘው የመጡ መሆኑን በዴክራላሪስዮን ቁጥር ሲ-5-7119 ሐምሌ 29 ቀን 1999 ዓ.ም እንዳስመዘገቡ ገልፀው ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ወደዱባይ ሊሄዱ ሲሉ 2500 የአሜሪካን ዶላር ብቻ የመለሱልኝ ሲሆን 10,000 የአሜሪካን ዶላር አስቀርተዋል፡፡ ስለዚህ ዶላሩን በአይነቱ ወይም በኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ እንዲከፍል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች አንድ ኢትዮጵያዊ ከ45 ቀናት በላይ የውጭ ገንዘብ መያዝ አይችልም ለጊዜያዊ ጉብኝት የመጣ ሰው ቢሆንም እንኳን ያመጣውን የውጭ ምንዛሬ ይዞ እንዲወጣ የሚፈቀድለት በአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ውስጥ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ይዘው እንዳይወጡ መከልከሉ ተገቢ ነው ሆኖም ዶላሩን በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት 10,000 የአሜሪካን ዶላር የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሠረት በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ ከየካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ በላከው መመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜያዊነት ለጉብኝት የመጡ ወይም ለንግድ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ሰዎች ለጊዜው በእጃቸው የያዙትን የውጭ ምንዛሬ ለጉምሩክ አስመዝግበው ማስረጃ ከያዙ ለአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ይዘውት የመጡትን የውጭ ምንዛሬ ይዘው ለመውጣት ፈቃድ አያስፈልጋቸውም የሚል በመሆኑ የተጠሪ ዶላር

የተያዘው በዚህ መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ የተያዘው ዶላር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው 10,000 ዶላሩን ጉምሩክ በሰጠኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ /Temporary Receipt for Deposit/ ቁጥሩ 176828 ገቢ ያደረግሁት በመያዣ ስም መሆኑንና ደረሰኙም ከአንድ መቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ እንደማያገለግል ይገልፃል፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕጋዊ መንገድ አሣውቀው ያስገቡትን ዶላር እንዳይወጣ ከሚከለክል በስተቀር የሚወርስበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ በመጣስ ዶላሩን ሊያወጡ ሲሉ የተያዘ በመሆኑ የመውረስ ሥልጣን አለን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ ከአሜሪካን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የግል ንብረታቸው የሆነውን 12,500 /አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ የአሜሪካን ዶላር አመልካች እንዲያውቀው በዲክራላሲዩን ያስመዘገቡ እና በጊዜያዊ የመያዣ ማስቀመጫ ደረሰኝ 176828 ያስያዙ መሆኑን በግራ ቀኙ ክርክር ተገልፆአል፡፡ ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ይዘው የመጡትንና ለአመልካች በግልጽ ያሣወቁትን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ ይዘው ለመውጣት የሞከሩ መሆኑንና አመልካች የብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ያለ ፈቃድ አንድ ሰው ለንግድ ወይም ለጉብኝት ወደ አገር ይዞት የገባውን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ሶስት ቀን በኋላ ይዞ መውጣት የማይፈቀድለት መሆኑን በመግለጽ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ተጠሪ ይዘው እንዳይወጡ የከለከለና ዶላሩን የያዘ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ለመንግሥት አሣውቀው ይዘው የገቡትን 10,000 የአሜሪካን ዶላር ከአንድ ዓመት ከአራት ወር በኋላ ያለ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ይዘው መውጣት እንደማይችሉ በመግለጽ መከልከሉ ተገቢነት ያለው ተግባር ቢሆንም ተጠሪ የውጭ ምንዛሬውን ይዘው የመወጣት መብታቸውን ከሚያጡ በስተቀር ዶላሩ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዳይሰጣቸውና በሕጋዊ መንገድ ከአገራቸው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ የወንጀል ተግባር ያልፈፀሙ በመሆኑ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ